ዐሥራ ዐምሥት

የመልስ ጉዞ ወደ ጊሻ/ዘንገና/

ከሁለት ቀን በኋላ ጉዞዬን ከጎንደር ወደ ባህርዳር ከዛም ወደ እንጂባራ አልፎም ዘንገና ሃይቅ አደረግሁ:: በቅርቡ ትምህርት ስለሚጀመር ቶሎ ብዬ ማወቅ ያለብኝን ለማወቅ እያሰብሁ ነበር:: ዘንገና አካባቢ እንደደረስሁ ከባህር-ዳር መስመር ሰሄድ በስተ ግራ በኩል በእግሬ በጠባቡ የኮሮኮንች መንገድ ወደ ውስጥ ተጓዝሁ:: ገብርኤል ቤተ-ክርስቲያን ደረስሁ:: ረፋድ ስለሆነ ሰዎች ብዙም አይታዩም:: ከዚህ በፊት ከማውቀው ቤተ-ክርስቲያን ውጭ ሌላ ምንም የሚጨበጥ የሚዳሰስ አዲስ ለውጥ አጣሁ:: ከቤተ ክርስቲያኑ አጥር ውጭ ተሳልሜ ወደ ሀይቁ ዳር ለዳር ማንም ሰው ተው አትጠጋ ሳይለኝ ብቻዬን ጥግ ጥጉን እሩቅ ተጓዝሁ::

ንፋሱ አየሩ ያስደስታል:: የሰላም ንፋስ የሚነፍስበት አካባቢ ነው:: ሀይቁ ውስጥ አልገባሁም:: ብዙ ደቂቃዎችን ተጓዝሁ አንድ ጥግ ላይ በጣም ትልቅ ከውሃ የወጣ የሚመስል ድንጋይ /አለት/ በእርቀት ተመለከትሁ:: ተጉዤ ደረስሁ አጥር በሚመስል መልኩ በተሰባበሩ እንጨቶች ተከቧል:: እንጨቶችን ተሻግሬ ገባሁ። አለቱ የተወለወለ የሚመስል ጥቁር ነበር:: ከውሃ ውስጥ የሚወጡ አለቶች አይነት ነው:: እንደ ተራራ ተገትሮ ሳየው መጽሐፉ ላይ ያነበብሁት ትዝ አለኝ:: መጽሐፉ ላይ ስለዚህ እንዳነበብሁት ጉብታ ላይ ያለ ግዙፍ ድንጋይ ነበር:: ተጠጋሁት... ዓይኔን እሱ ላይ ተክዬ አፈጠጥሁ:: አስተዋልሁት ከአካባቢው የተለየ እና ከወንዝ ውስጥ የወጣ ድንጋይ ነው:: ምናልባት ይሄ ይሆን ባኮስ ላይ በቅናት የጫኑት ድንጋይ? ለታሪክ ምስክርነት ተቀምጦ ይሆን? እንዴት በዘመናት

ሂደት ሳይለወጥ ሰዎች ወደ እሱ እንዳይሄዱ መንፈስ አለ እየተባሉ ለሊያም ሌላ ሳይበላሽ ቀረ ሰዎች እንዴት ሳይደርሱበት ቀሩ? ከውሀ ውስጥ ይሄን ድንጋይ ማውጣት ከትልቅነቱ አንፃር ለሰው ልጅ ከባድ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። መጽሐፉን ሙሉ በሙሉ አምኛለሁ። በጊዜው ምን አይነት አጋሰሶች እና ዝሆኖች ተሸከሙት? በጣም ይገርማል ትልቅ እንደ ተራራ የተገተረ ከባድ የሚመስል ድንጋይ ነው። አፍጥጬ እየተመለከትሁት ሳለ አንድ ሰው ከሩቅ እየጮኸ...

"አባት አባት እሱን ድንጋይ እንዳትቀርብ እስከሱ ምን ልታደርግ ገባህ? ውሀው ውስጥ መግባት አይቻልም ጠበል ነው ወደሱ ከተጠጋህ ትሞታለህ።" እያለ ሰማሁት። ፊቴን ወደ ሰውዬው አዞርሁ እና ተመለከትሁት። ወደ ኋላ ሸሸት አልሁ። እንደ ከዚህ ቀደሙ ልቤ አልተሰወረም። ድንጋዩን ተመለከትሁት ሰውየው ወደ እኔ ተጠጋና....

"ከዚህ ያለፈ ማንኛውም ሰው ይሞታል። ትሞታለህ ደግሞስ እዚህ ቦታ ቀትር ላይ ብቻህን ምን ታደርጋለህ?" አለኝ። ዳግም ከዚህ በፊት ወደ ሀይቁ ስሄድ ያወጣኝ ሰው ትዝ አለኝ። ሰውየው አሁንም እየተመለከተኝ ነበር።

"በቃ ተመለስ ወደ እዚህና" አለኝ። ካለሁበት መንቀሳቀስ አልፈለግሁም። እዚህ ቦታ ላይ የቆሙ ቅዱሳን ምን በእጃቸው እንደነበር እንዳነበቡ ባላውቅም ህይወትን እንጅ ሞትን ስለማያውቁ ልርቅ አላሰብሁም። ሰውየው ...

"በል ከዚህ ቦታ እንዳታልፍ ወደ ውሀው ነው የሚወስድህ ተመለስ እሽ!" አለኝ

"እሽ አልሄድም" አልሁ

'በላ ና እንሂድ" አለኝ

"እሺ አልሄድም እዚህ ላይ ትንሽ ልቆይ!" መለስሁለት። እንደ ቀደመው ሰውዬ ካልወሰድሁህ አልሄድም አላለም። እኔ ሌላ ጥያቄ አልጠየቅሁትም። ውሃው ቅዱስ ውሃ መሆኑን ግን ባነበብሁት

በመጽሐፉ አሁንም ሲናገር ተረድቻለሁ። ቀድሞ ስመጣ ሳላውቅ ነው ወደ ውሃው የገባሁት... ደግሞም በወቅቱ በሰዎች ጅኒ፣ ሰይጣን፣ አስፈሪ ነገር እንዳለበት ነበር የሚታመነው።

"በቃ እሽ ከዚህ እንዳትርቅ ተመለስ መልካም ቀን።" አለና ጥሎኝ ሄደ። እኔ ግን እሱ እንደራቀኝ እርግጠኛ ስሆን በፍራቻ ሁኜ ጫማየን በማውለቅ በቅርብ አስቀምጬ። ወደ ደንጋዩ ተጠግቼ አካባቢውን እየቃኘሁ ቆየሁ። እየፈራሁ ነበር... የሰውየው መሄድ እርግጠኛ ስሆን ተነስቼ ወደ ድንጋዩ ስር አመራሁና ተመለከትኩት። ድንጋዩን አለፍሁትና ተጓዝሁ... ምንም የሚታይ ነገር የለም። ወደ ውስጥ ገባሁ ዘንገናን ሀይቅ ዙሪያውን ዛፎች ከብበው ይታያሉ። ልቤን እየደከመኝ ነበር። ወደ ድንጋዩ ተመለስሁና ድንጋዩን እቃኘው ጀመር። ምንም ነገር አላየሁም።

ምናልባት ደንጋዩ ላይ የሆነ ነገር አገኛለሁ በሚል ደንጋዩን አፍጥጬ ተመለከትሁ። ከታች፣ ከጎን፣ ከኋላ፣ ከፊት፣ ከስር እና ከላይ በረበርሁት። ምንም ነገር አልነበረው። ድካሜ ምንም ነገር ሳያፈራ በሄድሁበ. ሁሉ ምንም ነገር ሳላገኝ ከጉቱ እንደ ነበር ተሰማኝ። የሞትን መድኃኒት /ዕጸ ህይወት/ መጽሐፍንም እንዳላገኘሁ ሳስብ ምንም ፍራት በውስጤ ሳይኖርብኝ ሳልጨነቅ ከዚህ በቀጣይላ ከእነዚያ ሁለት አባቶች ስለሰረቅሁት የዚያ መጽሐፍ ሚስጥር ለአባ ባህሪ ላጋራቸው ምናልባት ሚስጢሩን እሳቸው ያስፈቱት እንደሆን ልሰጣቸው ወሰንሁ። ቀድሜ ግን ስለ አባ ጊዮን ታሪክ ካወቅሁ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ። እስከ አሁንየምሰማው ዝም ብሎ የፈጠራ ታሪክ ይሆናል ብዬ ስላሰብሁ ካለፍርሃት ደንጋዩ ላይ ወጥቼ ተቀመጥሁ። በጣም ደከመኝ እንቅልፍ ሊወስደኝ እያናወዘኝ ሳለ ደንጋዩ ላይ አንድ የእጅ የሚመስል ዱካና አስር ጣቶችን ተመለከትሁ። ሰፊ መዳፍ ነው ደነገጥሁ። ምንድን ነው እራሴን ጠየቅሁ ብዙ ሳልቆይ ይሄ አስታወስሁ። ለምልከትነት የተቀመጠው የባኮስ የእጅ ጣት ነበር? ይሄ ነገር እውነት ይሆን?

ለራሴን ጠየቅሁ እውነት ነው:: በአስተውሎት ተመለከትሁት ሰፋፊ ሁለት አምስት አምስት ጣት ያላቸው ረጃጅም እጆች ጥቁሩ ደንጋይ ላይ ተነጥፈዋል:: ደንጋዩ ተፈጥሯዊ እንጂ በእጅ የተሰራ አልነበረም:: የተፈጥሮ ከውሀ የወጣ የሚመስል ደንጋይ፣ ደንጋዩ ገና ሲፈጠር ሳይደርቅ የሰው እጅ ያረፈበት ነው የሚመስለው:: እውነት የባኮስ የእጅ ቅርጽ ይሆን? እውነት ባኮስ ይሄን ድንጋይ ነው ፈጣሪ ኃይል ሰጥቶት በእጁ ከላዩ ላይ ያንከባለለው? አልሁ መጽሐፉ ላይ ያለውን ነገር በአካል በማየቴ ግራ ያጋባል:: ዝሆኖች እና አጋሰሶች ሲጎትቱት በጣም እየከበዳቸው ነበር:: ሲጎተትና ሲጫን የሚያሳይ እንደ እጁ ያለ ቅርጽ ሊኖር ይገባል:: ቢሆንም ከእጅ አሻራው ውጭ ምንም ምልክት የለም:: ያም ሆነ ይሄ ደንጋዩ የተወለወለ አለት ጥቁር መስታወት ሲመስል፣ ደንጋይ እንደመሆኑ የተለያየ ቅርጽ ቢኖረውም ከአሻራው ውጭ ምንም ነገር አልተቀረጸበትም:: የፈጣሪ ስራ ድንቅ ነው:: ደግሞም ከመጽሐፉ ካለው ቅርጽ ውጭ ድንጋዩ ባኮስ ላይ የተጫነው ስለመሆኑ ማስረጃ የለኝም::

እንቅልፍ እያናወዘኝ ቢሆንም ተጣጥሬ በእጆቼ በጣቶቼ ልክ እላያቸው አሻራዎቼን አሳረፍሁ ነካኋቸው:: ያኔ እጄ ያረፈበት ብቻ ወደ ውስጥ ሲሰጥም እና ድንጋዩ ሲከፈል ተሰማኝ ደነገጥሁ:: ለመነሳት አስቤ ነበር ኃይል አጣሁ:: ልቤ ሲሰለብ ጭንቀት እና ድካም ሰውነቴን አዛለው:: በድኔ ሌላ ቦታ ሰውነቴ እዚህ እንደሆነ ይሰማኛል:: አንድ የተጠቀለለ ብራና የተመለከትሁ መሰለኝ:: ደስ አለኝ ላነሳው አሰብሁ:: እያየሁት ነበር ከላይ በግእዝ "ኖኃተ ህይወት" ወደ አማረኛ ሲቀየር "የህይወት በር" የሚል ነገር ተጽፎበት አየሁ:: የምፈልገው መጽሐፍ ይሄ ነበር:: ከደንጋዩ ውስጥ ያለው መጽሐፍ ከደንጋዩ ጋር ግንኙነት የሌለው እንደሆነ አስተውያለሁ:: አንድ ገጽ ገልጬ አየሁ ወደ ታች ሰባት ቃላት የተጻፈ ነገር ተመለከትሁ:: ቃሉ የግእዝ አይደለም ግን ፊደሎቹ የግዕዝ ናቸው:: አውጥቼ አልተመለከትሁም:: አነበብሁት...

ፎዞ ኤል
ሆሎ ኤል
ሞዶ ኤል
ቆቶ ኤል
ሶቦ ኤል
ጮቫ ኤል

ዎጴ ኤል በቃሌ እነዚህን ቃላት ደጋግሜ ስናገር መጽሐፉ ተገለጸ ማንበብ ቀጠልሁ:: ደንጋዩ ላይ እንደ እንቅልፍ ያለ ነገር ጣለኝ:: በህልም በሚመስል ዓለም ውስጥ ገባሁ:: ስለ እነዚህ ቃላት በእንቅልፍ ውስጥ አወራለሁ:: ቃላቶቹ የግእዝ እና አማረኛ የመጨረሻ ቃላትን እንዲሁም "ኤል" የሚል የፈጣሪ ስም ይዘዋል:: የፈጣሪን ስምን የያዙ መሆናቸውን እየፈታሁ ሳልጨርስ ደቂቃዎች ነጉደው ሌሎችን ያነበብኋቸውን ገጾች ሳልፈታ ከወሰደኝ እንጉልች እና እንቅልፌ በጥንካሬ ነቃሁ:: ጥቁሩ ደንጋይ ከአካባቢዬ የለም:: እንደ በፊቱ ከላዩ ላይ አልተቀመጥሁበትም:: የሆነ የዋርካ ዛፍ ስር ነበር:: ያለሁት የ' ነው? ራሴን እየጠየቅሁ ባለሁበት ሰዓት... አንድ ፂማቸው እና ጸጉራቸው ተንዣርግጎ ከአይናቸው እና ከንፈራቸው ውጭ የማይታዩ በነጭ ጸጉር ያሸበረቀ አባት ፊት ለፊቴ ተቀምጠዋል:: ደንግጬ አማተብሁ...

"አይዞህ ልጄ አትደንግጥ ::" አሉኝ::

"እንዴት አባ?" መለስሁላቸው

"አልሞትህም ለጊዜው ተሰውረሀል" አሉኝ::

"ምን ማን እኔ?" ግራ ገባኝ...

"አዎ አንተ አሁን ለሁሉም ሰው ተሰውረሃል::" እኔ መሰወርን አላስብም አልፈልግም ስለ መሰወር ምክንያት የሆነውን መጽሐፍ ለማወቅ ጓጉቼ እንጂ... አስደነገጡኝ::

"ለይሆንም ለይሆንም ለይሆንም እርሶ ማን ኖት?" አልሁ በፍርሀት ውስጥ ሆኜ ያሰብሁት ሁሉ ሳይሆን በመቅረቱ ግራ ተጋባሁ ጨነቀኝ ::

"እኔ አባ ፍቅረ ሥላሴ ነኝ" አሉኝ:: ደነገጥሁ ይሄን ስም ቅዱስ ያሬድ ተሰወረበት በተባለው አካባቢ በነበርሁበት ጊዜ በዛ ገዳም ያሉት እኒያ አባት የነገሩኝ ስም ነበር:: እኒህ አባት አባ ጊዮን/ ፍቅረ ሥላሴ/ ናቸው::

"እንዴት ግን?" ጠየቅኋቸው

"መሆን ስለምትፈልግ" መለሱልኝ

"አይ አልፈልግም እኔ መሰወር አልፈለግሁም" አልኋቸው:: እየፈራሁ ውስጤም መሰወር አይፈልግም:: ምድር ላይ ብዙ የሚጠብቀኝ ነገር አለ::

"ሆኗል አንተም የዚህ ሚስጥር ተጋሪ ነህና ለጊዜው እንደ ሰው ላትታይ ተሰውረሀል::" አሉኝ ግራ ተጋባሁ አካባቢውን ቃኘሁት:: አካባቢውን አስተዋልሁ:: ይመስለኛል እርቄ አልራቅሁም ዘንገና አካባቢ እንዳልሁ ይሰማኛል:: ግን የት? አሁንም አላውቅም ወደዚህ የገባሁበትን መንገድ እያስታወስሁ ነበር:: ሳላውቅና ሳላስብ ባገኘሁት ሳቢ መጽሐፍ የተነሳ ወደ እዚህ መስመር ቀስ እያልሁ ገባሁ::

"ከእንግዲህ ወደ ኋላ መመለስ የለም ተከተለኝ::" አሉና እጄን ያዙኝ:: አያያዛቸው ከጠንካራ ወጣት በላይ ነው እጃቸው ብረት ነበር::

"አባ እኔ መሰወር አልፈልግም ለመሰወር ምክንያት የለኝም::" መለስሁላቸው ጨንቆኝ በፍርሃት ውስጥ ሆኜና ግራ ተጋብቼ::

"እሱስ ለዛም አልደረስህም ሁሉን እንድታውቅ ግን ተሰጥቶሀል::" አሉና መለሱልኝ::

"ስለምን?" ጠየቅኋቸው



“ታየዋለህ” አሉኝ ትንሽ ተጉዤ የሆነ ቁልቁል ወደ ታች ሲያዩት የተገተረ ተራራ ታቹ በሹል ድንጋይ የተወረረ የሚመስል። ቁልቁል አስፈሪ ገደል ተመለከትሁ። ቁልቁል ከተራራው ወደ ታች ያለ ምንም ድጋፍ እንድወርድ እጄን ጎተቱኝ። ግራ ተጋባሁ እሳቸውን ልከተል ነውስ? ፈራሁ። ከዚህ ወድቄ እንዴት ባለ አስከፊ ሁኔታ እንደምሞት አሰብሁ መሞት አልፈለግሁም። ተጨነቅሁ በጠንካራ እጃቸው ሰበው ከእሳቸው አስከተሉኝ። ቁልቁል ከተራራው ወደ ታች በጩኸት ያለ ምንም ድጋፍ ወረድሁ። ግን እንደፈራሁት አልወደቅሁም። ተንሳፈፍን ጀርባዬን አየሁ ክንፍ የለኝም እኔ እንዴት እንደዚህ ሆንሁ። አላውቅም...

“ጮኹ አይደል አባ?” አልሁና አባፍቅረ ሥላሴ ፍርሀቴ ሲቀንስ ጠየቅኋቸው።

“ማንም አይሰማህ አታስብ ለተወሰነ ቀን ዓለምን ታያለህ እንጅ ዓለም አንተን አያይም አይሰማምም...” አሉኝ። ግራ ያጋባል አብረን ወደ ታች እየተወረወርን ነበር። ወደ መናፍስት እና ወደ ተሰወሩ አባቶች ዓለም እንደሚሆን እርግጠኛ ነበርሁ። በዚያ ዓለም መልከ ፄዴቅ፣ኤልያስን፣ ሄኖክን፣ ያሬድን፣ ባኮስን፣ ኒቆዲን፣ ዲዲሞስ፣ ያሬድ፣አስጢዮስ፣ አቡነ አረጋዊ ና ሌሎችን የማገኝ መሰለኝ አዲስ ህይወት...

ዐሥራ ሥድሥት

የመሰውረ - ዓለም

መቼ እና የት እንደሆነ አላውቅም በብርሀን የሚመጣ የአባ ጊዮን የሚመስል ድምጽ...

“ልጄ አንተ የሞትን መድኃኒት እስከ ዘለዓለም የመሰወሪያ ጥበብን ፈለግህ፣ መጽሐፉን አገኘህ እንጅ በህይወት ለመኖር ላለመሞት አልፈለግህም። ይሄን አንተ ብቻ ሳትሆን ዓለምም ትፈልገዋለች በህይወት ለመኖር ለመሰወር ብትፈልግም ለመኖር ብዙ ደረጃዎችን ማለፍ ነበረብህ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ብዙ ስራዎች ይጠበቁብህል። ይሄን ደረጃ አንተ አልደረስህም። ብዙ ደረጃዎችን ስታልፍ ሁሉ መንገድ ከፍት ነው። አባቶች ከመሰወራቸው በፊት የህይወትን መጽሐፍ አንብበው በህይወት የኖሩት እነዚህን ደረጃዎች አልፈው ነው። አንተ ደረጃዎችን ሳትደርስ ከሞት መሰወሪያውን መጽሐፍ አነበብህ የዚህ ታሪክ ተካፋይ ሆንህ። ግን ያላለፍህቸው ደረጃዎች አሉና አትኖርም ከእኔ በስተቀር ቅዱሳንንም አታይም። የሰው ልጅ ተወልዶ፣ ተንከባልሎ፣ ድክድክ እንደሚል ሁሉም ደረጃዎች አሏቸው... እነዚህ አባቶች እዚህ ለመድረስ በቅድስና እነዚህን ደረጃዎች አልፈዋል።

1. ጽማዌ፦ በዓለም ያለውን ማንኛውንም ድምጽ አለመስማት የልብን ሐሳብ ብቻ ማዳመጥ በሕሊና ነገረ እግዚአብሔርን ማሰብ ነው።

2. ልባዌ፦ ልብ ማድረግ፣ ማስተዋል፣ ማወቅ ነው።

3. ጣዕመ ዝማሬ የሚጸልዩትን ጸሎት አንድ በአንድ ምስጢሩን ማወቅ ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት አለመሰልቸት ዝማሬ መላዕክት መሆን::

4. አንብዕ (አንብዐ ንስሐ)፡- ቅዱሳን የዕንባ ሀብት ይሰጣቸዋል:: በእግዚአብሔር ፊት ሳያቋርጡ በአለም ስለሚሆነው መጥፎ ነገር ሁሉ ያነባሉ (አንብዐ ንስሐ) ያገኛሉ::

5. ኩነኔ፡- የነፍስ ፈቃዳቸው የሥጋ ፈቃዳቸውን ይገዛል፤ ያሸንፋል፤ ለነፍሳቸው ይኖራሉ።

6. ፍቅር፡- አባቶች ሁሉን ሰው የመውደድ የማፍቀር ሀብት ይሰጣቸዋል:: እነርሱንም ሁሉ ይወዳቸዋል::

7. ሑሰት፡- በሌላ ቦታ የሚሠራውን ባንድ ቦታ ሆኖ ማየት መቻል ማለት ነው:: በዚህ ደረጃ አባቶች በአንድ ቦታ ተቀምጠው በአለም የሚሆነውን ያያሉ::

8. ንጻሬ መላእክት፡- መላእክትን በዚህ ዓለም ሆነው እያዩ ነፍስ ግን ለተወሰነ ጊዜ ከመላእክት ጋር እግዚአብሔርን እያመሰገነች በጣዕመ ዝማሬ ተመስጣና ተደስታ ከቆየች በኋላ ትመለሳለች::

9. ተሰጥሞ፡- ዓሣ በባሕር ውስጥ ተሰጥሞ እንደሚኖር፤ እዚህ ማዕርግ ላይ የሚደርሱ አባቶች ኅሊናቸው ጸጥ ይላል፤ ልዑል፣ ስፉሕ፣ ረቂቅ በሚሆን ብርሃን ይሰጥማሉ (ይዋኛሉ)፤ ሕይወታቸው ብሩህ ይሆናል፤ ሙሉ በሙሉም ደስተኞች ይሆናሉ::

10. ከዊነ እሳት፡- ቅዱሳን ከከዊነ እሳት ማዕርግ ሲደርሱ እንደ እሳት ይሆናሉ:: ሰውነታቸው በብርሃን ይከበባል፤ ከእግር እስከ ራሳቸው ድረስ እሳት ይመስላሉ::

እነዚህን ማዕረጋት ስታልፍ ያኔ አይንህ ይበራል:: ይሄን መጽሐፍም ርዕሱን እና ላዩን ሳይሆን ውስጡንም ታያለህ ለህይወትህም ይሆናል::" የሚል ድምጽ በጀሮዬ እየፈሰሰ ቀስ በቀስ

ከወለደኝ እንቅልፍ የመሰለ ነገር ተነሳሁ:: በትንሹ ዓይኔን እየከፈትሁ...

አይኔን ከፍቼ ፀሀይን ለማየት ሞከርሁ:: ቀድሞ የለበስሁት ልብስ እና የያዝሁት ዕቃ ሙሉ በሙሉ በእጄ አለ:: ከኪሴ ስልክ አውጥቼ ሰዓት ተመለከትሁ:: ሰምንት ሰዓት ሆኗል:: ፊት ለፊቴ ከጫካው ውጭ ማንም ሰው አጠገቤ የለም... አባ ጊዮን/ፍቅረ ሥላሴ/ም የሉም...

አይኔን አፈጠጥሁ የተቀመጥሁት ገጠር ውስጥ በሸተኞችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመውሰድ ሰዎች በሚጠቀሙበት ወሳንሳ ላይ ነው:: ምን ሆኜ ነው? በራሴ ሀሳብ ውስጥ እንዳለሁ የሆነ ሰው ወደ እኔ ፈጥኖ መጥቶ እያስተዋለኝ እና በስስት እየተመለከተኝ ...

"ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን ድኗል ድኗል" አለና ጮኸ በአካባቢው ያሉ ጥቂት ሰዎች መጥተው ከበቡኝ:: ከመንገዱ ዳር ነበርሁ:: ከወሳንሳው ተነስቼ ቆምሁ:: በአካባቢዬ በዛ ያለ ሰው ተሰበሰበ ሁሉም ፈጣሪን አመሰገኑ:: ደንግጫለሁ ቀስ በቀስ ወደ እራሴ ስመለስ ምን እንደሆነ ጠየቅኋቸው:: ከዘንገና ሀይቅ በቅርብ እርቀት ወድቄ አባቶች አግኝተውኝ ጅብ እንዳይበላኝ እዚህ በወሳንሳ አምጥተው ሶስት ቀናት እዚህ እንደተቀመጥሁ እየተጠበቅሁ ጸሎት እየተደረገልኝ እየተጠመቅሁ እንደቆየሁ ተነገረኝ:: ደነገጥሁ አሁን አባቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደሄዱ አወሩን:: እዛው ከነበርሁበት እንዳለሁ ሳያነሱኝ ብቆይ ጅብ እንደሚበላኝ አወጉኝ:: እንዳሉትም ባንኜ የተነሳሁ ቢመስለኝም ድካሙ መልሶ ቁጭ እንድል አስገደደኝ:: ከእነዚያ ሁለት አባቶች የሰረቅሁት መጽሀፍ ከለበስሁት ሱሪ ኪስ ውስጥ አለ:: ራሴን ከረሳሁ እና ከሳትሁ አራት ቀን ሆነኝ ማለት ነው::

አንድ አባት በፍጥነት ከአንድ ሰው ጋር መጡና አሳልመው ሰለ እኔ ጠየቁኝ:: ስለሆነው ሁሉ ምንም እንደማላውቅ ነገርኋቸው::



የሆነውን እና ከሰዎች የሰማሁትን ታሪክ በሙሉ ደግመው ነገሩኝ። ጠበል ሰጥተውኝ ጠጣሁና ባዶ ሆዴ ምግብ እንዲያገኝ አደረጉ። በላሁ...

"ልጄ ቤተ-ክርስቲያንን ንቀህ የደረሰብህን አየህ አይደል የትም ቦታ ያሉ ቤተ እምነቶችን የየትኛውም ሀይማኖት ቢሆኑ አትናቅ ሞተህ ነበር እኮ" አሉኝ። ተቀብያለሁ

"እኛም አንተን ለማንሳት አስቸግረኸን ነበር። ሰውነትህ እየተጣጠፈ ቅርፀ ቢስ ሆነህ ነበር እንደምንም ተባብረን ነው አፍሰን ያመጣንህ። አንተም ተጎድተህ ሰዎችንም ችግር ላይ ጥለሀል" አሉና ትከዝ አሉ። ስለ እኔ ጠየቁኝ ስለ ስራዬ እና ኑሮዬ አንዳንድ ጉዳዮችን ነገርኳቸው።

***

ዘንገና ሀይቅ፣ደኖቹ እና ቤተ ክርስቲያኑ በቦታቸው አሉ። ከሁለቱ አባቶች የወሰድኩት መጽሐፍ እጄ ላይ ነው። አባ ጊዮን ሁሉን አውቀህል ቢሉኝም መንገዱን እንጅ የተሰወሩበት ምክንያትን የተሰወሩ ሰዎች የት እንዳሉ፣ እንዴት እንደሚኖሩ? ስለመጨረሻ ዘመናቸው? አላውቅም። አገኛቸዋለሁ ያልኳቸውን አባቶች እና ነገሮች ሁሉ አላገኘሁም። ያወቅሁት ነገር ቢኖር አባቶች ከመሰወራቸው በፊት የፈጠራቸውን አምላክ በማመን አስሩን የማዕረግ ደረጃዎች አልፈው "የህይወት በር" /ኖኃተ ህይወት/ የሚለውን መጽሐፍ አንብበው እነዚያን ሰባት ቃላቶች ደግመው፣ መጽሐፉንም ገልጠው አንብበው መሰወራቸውን ነው። መጽሐፉን እየገለጽሁ ባነብም ስላነበብኳቸው ነገሮች አላስታውስም ሁሉም በአዕምሮዬ የለም። የፈለግሁትን ያወቅሁትን መጽሐፍ የሆነውን ሁሉ ነግሬ ከእጄ ቢሰወርም ከእነዚያ አባቶች የወሰድኩትን መጽሐፍ ለአባ ባህሪ ለመስጠት ወስኛለሁ። ሁሉም ነገር በባለቤቱ ያምራል።



ደሴ ከዳም

አስር ሰዓት ላይ የዘንገና አካባቢ ሰዎች እና አባቶች ተሰናብተውኝ ፈጣሪ መልሶ ህይወቴን ሰጥቶኛልና ፈጣሪን አመስግኜ የዛሬ ዓመት የአንድ ወር ደሞዜን ለመስጠት ቃል ገብቼ ጉዞዬን ጀመርሁ:: በሰዓቱ አልመሸም ነው መሰለኝ ወደ ህይቁ አዲስ ሙሽሮች እየገቡ ነበር:: የሚሄዱት ከህይቁ አጠገብ ፎቶ ለመነሳት ብቻ ነው:: ውህው አሁን ሰራዉን አግኝቷል:: ቅዱሱን ያዳነ ቅዱስ ውህ ነው እና... ለሙሽሮችም ሰርጋቸው የአብርሃም እና የሳራ እንዲሆን፣ ለዘንገና አካባቢ ሰዎችም መልካም ህይወትን ተመኝቼ መንገድ ዳር ስደርስ ወደ ባህር ዳር ይዞኝ የሚሄድ ታክሲ መጠባበቅ ጀመርሁ::

ዐሥራ ሠባት

ከዓመት በኋላ

ለአባ ባህሪ መጽሐፉን ከሰጠኋቸው አንድ ዓመት ሳይሞላ አንድ አባት እንደተሰወሩ ሰማሁ። እኒህ አባት በፍለጋዬ ላገኛቸው ያልቻልኋቸው አባ ሰላመ አብ ነበሩ። እንዴት? ለሚለው ጥያቄ መልሱን አግኝቻለሁ። ለምን? እና ምን ፈርተው? የሚለው ጥያቄ ግን እንደ ሰዎች ይወሰናል። እኛ አይሆንም እያልን የምንኖር ድንቅ ነገሮች፣ ጥበብን አቅፈንና ኑረውን ያንን ማንፈትሽ፣ ማንሞክር ሰዎች እንደሆንን አውቃለሁ። ዛሬ በህይወቴ ብዙ ነገሮች ተለውጠዋል። ብዙ ነገሮችም ተምሬያለሁ አባ ባህሪ እና ሌሎች አባቶች ሳያውቁ በሰራሁት ያልተገባ ስራ ምክንያት ዳግም የመጽሐፍ ማፈላለጉ ስራ ውስጥ እንዳልሳተፍ ላልተወሰኑ ዓመታት አግደውኛል። ማንአህሎሽ ከእስራኤል እኔው ጋር ጎንደር መጥታ አብረን መኖር ጀምረናል። ነገ ስለሚሆነው ነገ ለራሱ ያውቃል። ሰዎች የእግዚአብሔር ጸጋ ሲጎበኛቸው በዚያ ልምምድ ውስጥ ሲኖሩ ሄኖክ እንዳደረገው በቃላቸው የሚገባ የአፍ ፍሬን ሲሰጡ የህይወት በር መጽሐፍን ሲያነቡ እና ሲበሉ ሞትን አይቀምሱም ይሰወራሉ። እንግዲህ እግር አራሱን አያክም ከሚያውቁት መማር መስማት ነው። ወሬውን ከአባ ባህሪ ስለሰማሁ ምናልባት ከመጽሐፉና ከማውቀው ታሪክ ጋር ግንኙነት እንደሚኖረው ገምቻለሁ። ይሄን ነገር ለባለ ጉዳዮቹ ተውኩት...

-ተፈፀመ-